# የደን ጀኔቲክ ሀብት እንክብካቤ ፕሮጀክ

## የመጀመሪያ ምእራፍ

ከነሐሴ 1990 እስከ ሐምሌ 1993 ዓ.ም

**የሕይወታዊ ሀብት ጥበቃና ምርምር ኢንስቲትዩት**

German Technical Cooperation


አድራሻ:
ፖ.ሣ.ቁ 30726፣
ስልክ 612244 ወይም 09/207816፣
ፋክስ 613722 አዲስ አበባ ኢትዮጵያ


## የደን ሀብት ይዞታዎችን የመረጃ ማዕከል ማቋቋም

የኢትዮጵያን ደኖችንና በውስጣቸው ያሉትን የተለያዩ የደን እጽዋት ዝርያዎች በመጠንና በዓይነት ለመመዝገብና በተፈለገው ጊዜ መረጃዎቹን በቀላሉ ለመጠቀም የሚያስችል የመረጃ ማዕከል ሥራ የተጠናቀቀ ይገኛል:: የሚያስፈልጉት መረጃዎች ሁሉ ተጠናቀው ከገቡ በኋላ የደን እጽዋት ዝርያዎችን የአስተዳደግ ባሕርይና አጠቃላይ መግለጫ እንዲሁም ያሉበትን የእንክብካቤ ይዞት ከዚህ የመረጃ ማዕከል በቀላሉ ማግኘት ይቻላል::

## ቀጣይ ሥራዎች

የደን ጀኔቲክ ሀብት እንክብካቤ ፕሮጀክት ሐምሌ 1993 ዓ.ም የሚጠናቀቀው የመጀመሪያው ምዕራፍ ድረስ ከዚህ ቀጥሎ የተዘረዘሩትን ዋና ዋና ሥራዎች ያከናውናል::

- እፋጣኝ እንክብካቤ የሚያስፈልጋቸውን የደን እጽዋት ዝርያዎች መምረጥ
- የሕብረተሰቡን ግንዛቤ ለማዳበር በትምህርት መስጫ ተቋማትና ለተመረጡ የሕብረተሰብ ክፍሎች የተለያዩ ሴሚናሮችን ማካሄድ
- የደን ዘር ማከማቻ ቀዝቃዛ ክፍል /ጂን ባንክ/ ከአስፈላጊው ላቦራቶሪዎችና ቢሮዎች ጋር መገንባት
- የደን እጽዋት ዘሮችን በጂን ባንክ ማስቀመጥ
- የኢዘቦታ የእንክብካቤ ተከላ ቦታዎችን ማቋቋም
- የተፈጥሮ ደን የዘቦታ የእንክብካቤ ቦታ መከለልና መጠበቅ
- እየተካሄዱ ያሉትን ሥራዎች መቀጠል

6. ወንዶ ገነት የደን ኮሌጅ
7. ኬር ኢትዮጵያ /መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን በመወከል/

## በፕሮጀክቱ እየተካሔዱ ያሉ አበይት ሥራዎች

**በኢትዮጵያ ሀገር በቀል የዛፍና የቁጥቋጦ ዝርያዎች ላይ የተፃፉትን መረጃዎች ማሰባሰብ**

በሀገራችን ሀገር በቀል የዛፍና የቁጥቋጦ ዝርያዎች ላይ በተለያዩ ጊዜያት የተፃፉና ተበታትነው የሚገኙትን መረጃዎች አሰባስቦ ወጥነት ባለው መጽሐፍ መልክ ለማዘጋጀት እንዲያስችል ከተለያዩ ተቋማት የተውጣጡ የመስኩ ባለሙያዎች በአባልነት የታቀፉበት አንድ የሥራ ግብረኃይል ተቋቁሟል:: የደን ጀኔቲክ ሀብት እንክብካቤ ፕሮጀክት እስከአሁን ድረስ 838 የሚሆኑ የዛፍና የቁጥቋጦ ዝርያዎችን ዝርዝር ያሰባሰበ ሲሆን ከነዚህ ውስጥ 336 የሚሆኑት በሥራ ግብረኃይሉ አባላት ተወስደው ይህ ትራክት እስከተዘጋጀበት ቀን ድረስ የ238 ዝርያዎች መረጃ ተጠናቅሯል:: በዚህ ተግባር መሳተፍ ለምትፈልጉ ባለሙያዎች ሁሉ ጥሪያችንን እያቀረብን ይህንኑ ሥራ ለማቀላጠፍ ፕሮጀክቱ አስፈላጊውን ዋቢ መፃሕፍትና መጣጥፎችን እንዲሁም መረጃዎቹ የሚሞሉበትን ቅጽ ያዘጋጀ መሆኑን በአክብሮት እንገልፃለን::

## የደን እጽዋት ዝርያዎች ቅየሳ፣ ምዝገባና የማሕበረ ኢኮኖሚያዊ ጥናት

የደን ጀኔቲክ ሀብት ፕሮጀክት በተመረጡ የደን ይዞታዎች ላይ እንጨትነት ባህሪይ ያላቸው የደን እጽዋት ዝርያዎች ቅየሳ፣ ምዝገባና የማሕበረ-ኢኮኖሚያዊ ጥናት በቅርቡ ማካሔድ ጀምሯል:: ይህንን ጥናት ለማካሄድ 33 የተለያዩ የደን ሥርዓተ ምህዳሮች ተመርጠዋል::

## ኢትዮጵያ የስብጥር ማእከል ናት

ኢትዮጵያ 112.3 ሚሊዮን ሄክታር የቆዳ ስፋት ያላት ሀገር ስትሆን ወደ 60 ሚሊዮን የሚጠጉ የተለያየ ባህልና አኗኗር ያላቸጠው ሕዝቦች መኖሪያ ናት:: ጂኦግራፊያዊ አቀማመጧ በ$3^{0}24'$ እና $14^{0}53'$ ሰሜን ላቲትዩድ መካከል እንዲሁም በ$32^{0}42'$ እና $48^{0}12'$ ምስራቅ ሎንግቲዩድ መካከል ሲሆን ከባህር ወለል በታች 126 ሜትር ላይ ከሚገኘው የዳንከል ሸለቆ እንስቶ ከባህር ወለል በላይ 4620 ሜትር ላይ እስከሚገኘው የራስ ዳሽን ተራራ ድረስ ከፍታ ያላቸውን ቦታዎች አካታ ይዛለች:: ኢትዮጵያ ባላት ጂኦግራፊያዊ አቀማመጥ ብዛት ያላቸው የተለያዩ እፅዋትና እንስሳት ሀብት ባለቤት ስትሆን በዓለም አቀፍ ደረጃ የስብጥር ማእከልና የተለያዩ የእፅዋትና የእንስሳት ዝርያዎች መገኛ እንደሆነች ይታወቃል:: በኢትዮጵያ ውስጥ ከ7000 በላይ የእጽዋት ዝርያዎች ሲኖሩ ከነዚህ ውስጥ 12 በመቶ የሚሆኑት በኢትዮጵያ ውስጥ ብቻ እንደሚገኙ ይገመታል:: ወደ 1000 ከሚጠጉ እንጨትነት ባህሪይ ያላቸው የእጽዋት ዝርያዎች መካከል 300 የሚሆኑት የዛፍ ዝርያዎች እንደሆኑ ይታመናል::

የሀገሪቷ የደን ሀብት ይዞታ፣ ያለበትን ሁኔታ፣ ዝርያዊ ስብጥርና የመመናመን ደረጃን አስመልክቶ በቂ መረጃዎች የሉም:: የደኑን የእድገት ለውጥና በሥርዓተ ምህዳሩ ውስጥ ካሉት ሥነሕይወታዊና ግኡዝ አካላት ጋር ያለውን መስተጋብር በግልጽ የሚያሳይ መረጃም የለም:: በተጨማሪም በአንድ የዛፍ ዝርያ ውስጥ ሊኖር የሚችለው ተለያይነት ላይ ምርምር አልተካሄደም::

## የደን ሀብቶች መመናመን

ከኢትዮጵያ ከፍተኛ ወይም ጥቅጥቅ ደን በዓመት ከ150,000 እስከ 200,000 ሄክታር የሚገመት ደን መሬት እንደሚወድም ይገመታል:: የከፍተኛ ደን በዚህ ፍጥነት መመናመን የብዙ የእጽዋትና የእንስሳት መኖሪያ አካባቢዎችን መውደም በማስከተሉ ለሀገሪቱ ሕይወታዊ ሀብት መጥፋት መንስዔ ሆኗል::

በ19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን መግቢያ አካባቢ ከሀገሪቷ የቆዳ ሽፋን ውስጥ 35 በመቶ የሚሆነው በከፍተኛ ጥቅጥቅ ደን የተሸፈነ እንደነበረ የታሪክ መረጃዎች ይጠቁማሉ:: ዛፎች ዘርዝር ብለው የሚገኙባቸውን ሌሎች ሥርዓተ ምህዳሮች ጨምሮ በአጠቃላይ ወደ 66 በመቶ የሚጠጋው የሀገሪቷ ክፍል በደን የተሸፈነ ነበር:: ሀገር በቀል የሆነው የሀገሪቷ ከፍተኛ ጥቅጥቅ ደን በ1940ዎቹ ዓ.ም ወደ 16 በመቶ፤ በ1970ዎቹ ወደ 3.6 በመቶ፤ በ1980ዎቹ ወደ 2.7 በመቶ እንዲሁም በ1990 መግቢያ ላይ ከ2.5 በመቶ በታች አሽቆልቁሏል::

## የደን ጀኔቲክ ሀብት እንክብካቤ ፕሮጀክት ምሥረታ

የሕይወታዊ ሀብት ጥበቃና ምርምር ኢንስቲትዩት የሀገሪቱ ሕይወታዊ ሀብት እንዲጠና፤ በአግባቡ እንዲጠበቅ፤ እንዲበለጽግና ዘላቂ ጠቀሜታ እንዲሰጥ ማድረግና አፈፃፀሙን የመከታተል ብሔራዊ ኃላፊነት አለበት:: ይህን አብይ ዓላማ ከመተግበር አኳያና እየተባባሰ የሔደውን የደን ጀኔቲክ ሀብት ከጥፋት ለመታደግ ኢንስቲትዩቱ ከጀርመን ፌዴራላዊ ሪፑብሊክ መንግሥት በተገኘ የገንዘብና የቴክኒክ ድጋፍ ሐምሌ 1990 ዓ.ም የደን ጀኔቲክ ሀብት እንክብካቤ ፕሮጀክትን አቋቁሟል::

## የፕሮጀክቱ ግብ

የፕሮጀክቱ ግብ የደን ጀኔቲክ ሀብትን ኢኮኖሚያዊ፣ ማሕበራዊና አካባቢያዊ ጥቅም ዘለቄታ ባለው መንገድ ለማበልፀግና ለመንከባከብ በሚደረገው ሀገር አቀፍ ጥረት ጉልህና ግምባር ቀደም ሚና መጫወት ነው::

## የፕሮጀክቱ ዓላማ

የፕሮጀክቱ ዓላማ የደን ጀኔቲክ ሀብትን አግባብ ባላቸው ጽንሰሀሳቦችና ስልቶች በመመራት መጠበቅና መንከባከብ ነው:: ይህን ዓላማ ከግብ ለማድረስ እንዲያስችሉ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ዝርዝር ዓላማዎች ተነድፈዋል::

1. የኢትዮጵያን የደን ጀኔቲክ ሀብት ለመንከባከብ የሚረዱ ጽንሰሀሳቦችንና ስልቶችን መንደፍ
2. መንግሥትና ሕብረተሰቡ ስለደን ጀኔቲክ ሀብት እንክብካቤ አስፈላጊነት ያላቸውን ግንዛቤ ማዳበር
3. የአቅም ግንባታ ማከናወን
4. የዛፍ ፍሬዎች ለረጅም ጊዜ ሊቆዩ የሚችሉበት ማቀዝቀዣ ክፍል /ጂን ባንክ/ መገንባትና የዛፍ ዝርያዎች በተፈጥሮ ከሚገኙበት አካባቢ ውጪ የኢዘቦታ እንክብካቤ የሚውሉ የተከላ ቦታዎች ማቋቋም
5. የዛፍ ዝርያዎች በተፈጥሮ በሚገኙበት አካባቢ ተከልለው ወይም ተተክለው የሚጠበቁበትን የዘቦታ የተፈጥሮ ደን መንከባከቢያ ቦታ ማቋቋም ናቸው::

## ብሔራዊ የደን ጀኔቲክ ሀብት እንክብካቤ የሥራ ቡድን መቋቋም

ከሰኔ 15–16 ቀን 1991 ዓ.ም በተካሄደው የደን ጀኔቲክ ሀብት እንክብካቤ ስልት መቀየሻ ዓውደጥናት ላይ ብሔራዊ የደን ጀኔቲክ ሀብት እንክብካቤ የሥራ ቡድን ተቋቁሟል:: የሥራ ቡድኑ ዋና ዓላማዎች ለደን ጀኔቲክ ሀብት እንክብካቤ ፕሮጀክት የቴክኒክ ድጋፍ መስጠትና ፕሮጀክቱ የሚመራባቸውን የሥራ ዘዴዎችና ስልቶች መመርመርና ማጽደቅ ነው::

ይህ የሥራ ቡድን ከፕሮጀክቱ ዓላማ ጋር አግባብ ካላቸው ሰባት ተቋማት በተውጣጡ 12 ከፍተኛ ባለሙያዎች የተገነባ ነው::

በሥራ ቡድኑ የተወከሉ ተቋማት

1. የሕይወታዊ ሀብት ጥበቃና ምርምር ኢንስቲትዩት
2. አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
3. የኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ድርጅት
4. የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን
5. ግብርና ሚኒስቴር